

# የአስከሬን ምርመራ መረጃለRECOVER የሰውነት አካል ምርመራ ስምምነት ቅጽ

RECOVER
Researching COVID to Enhance Recovery

*An Initiative Funded by the National Institutes of Health*

RECOVERcovid.org

# በ RECOVER ጥናት ላይ ላሳዩት ፍላጎት እናመሰግናለን።

በወዳጅዎ ሞት በጣም አዝነናል።
aበማይቻል መንገድ ስለ COVID የረጅም ጊዜ የጤና ችግሮች እንድንማር ሊረዳን ይችላል።



## የአስከሬን ምርመራ ምንድን ነው?

የአስከሬን ምርመራ ከሞት በኋላ የሚደረግ የሰውነት ሕክምና ምርመራ ነው። አንድ ሰው እንዴት ወይም ለምን እንደሞተ የበለጠ ለማወቅ አንድ ሐኪም (ፓቶሎጂስት ተብሎ የሚጠራ) በሆስፒታሉ ውስጥ የአስከሬን ምርመራ ያደርጋል።

## የአስከሬን ምርመራዎች ለምን ይደረጋሉ?

የአስከሬን ምርመራ የሞት መንስኤ ምን እንደሆነ ለመረዳት እና ግለሰቡ አንዳንድ በሽታዎች የነበሩበት እንደሆን ለማወቅ ይረዳናል።

# RECOVER የአስከሬን ምርመራ (እንዲሁም የሰውነት ፓቶሎጂ ጥናት ተብሎ የሚጠራ) የሚያደርገው ለምንድን ነው?

በዚህ ጥናት ውስጥ፣ ለምን አንዳንድ በኮቪድ የተያዙ ሰዎች እንደሚሻላቸው፣ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ለረጅም ጊዜ ታመው እንደሚቆዩ መረዳት እንፈልጋለን። እንደ የRECOVER ጥናት አካል፣ ተመራማሪዎች የሚከተለውን ለመማር በሞተ ሰው ላይ የአስከሬን ምርመራ ያደርጋሉ፦

- COVID የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን እንዴት እንደሚጎዳ
- የ COVID የረጅም ጊዜ ጉዳቶች

እንዲሁም ተመራማሪዎች በሞተው ሰው የጤና መዝገብ ላይ ያለውን መረጃም ይመለከታሉ።

# የአስከሬን ምርመራ ስራ ላይ ምን ይከናወናል?

ሐኪም (ፓቶሎጂስት ተብሎ የሚጠራ) ከሞት በኋላ የውጪ እና የውስጥ ሰውነትን ይመለከታል። ከሕብረ ሕዋሳት እና ከአካል ክፍሎችን ለማጥናት ትንሽ ናሙና በአክብሮት ይሰበስባሉ፣ ለምሳሌ፦

- ደም ወይም ሌሎች ፈሳሾች፣ ለምሳሌ የአከርካሪ ፈሳሽ
- አይኖች
- አንጎል
- ልብ
- ሳንባዎች
- ጉበት
- ስፕሊን
- ጣፊያ
- ኩላሊቶች
- ፊኛ
- በሆድ ውስጥ ያሉ አካላት፣እንደ ሆድ ወይም ትልቁ አንጀት ክፍል(ኮሎን)

የተወሰኑ የሰውነት ክፍሎችን ብቻ እንዲመለከቱ (ለምሳሌ፣ ጭንቅላትን የማያጠቃልል ከደረት እና ከሆድ ብቻ) ፈቃድ ለመስጠት መምረጥ ይችላሉ። ነገር ግን፣ ይህ የሞቱ ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል እና የአስከሬን ምርመራው ለRECOVER ምርምር ጥቅሙ አነስተኛ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።



# ከአስከሬን ምርመራ በኋላ ምን ይሆናል?

እንደ የምርምር ጥናት አካል፦

1. ሐኪሙ ለምርምር የሚያስፈልጉትን ናሙናዎች ልዩ ቁጥር ይሰጣሉ፣ ስለዚህ ግለሰብን መለየት የሚያስችላቸው መረጃ አይኖራቸውም።
2. ከዚያ ለክፍት የሬሳ ሣጥን የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ ወይም አስከሬኑ ሊታይ ለሚችልበት ሌላ ሁኔታ አስክሬኑን በጥንቃቄ እና በአክብሮት ያዘጋጃሉ።
3. በኋላ ላይ ምርመራ እንዲደረግባቸው ናሙናዎቹን ወደ ላብራቶሪ ለማስቀመጥ (ባዮሬፖዚቶሪ ተብሎ የሚጠራ) ይልካሉ።





## ከአስከሬን ምርመራው ውጤት አገኛለሁ?

ህጋዊ የቅርብ ዘመድ ከሆኑ፣ የአስከሬን ምርመራ ውጤቱን ሪፖርት ሊያገኙ ይችላሉ።

ሐኪሙ ከአስከሬን ምርመራው የተማሩትን ሪፖርት ይጽፋሉ፣ ይህም ከታወቀ፣ የሞቱን ምክኒያት ያካትታል።

ምንም እንኳን አንዳንድ ሪፖርቶች ብዙ ጊዜ ሊወስዱ ቢችሉም፣ በአብዛኛው ሪፖርቶች በ60 የስራ ቀናት ውስጥ ይገኛሉ።

ውጤቶቹን ለማብራራት ሊረዳዎ ከሚችል ሐኪምዎ ጋር ይህንን ሪፖርት እንዲመለከቱ አበክረን እንመክራለን።

ሪፖርቱ ከRECOVER ጥናት የተገኙ የምርምር ግኝቶችን አያካትትም፣ ለምሳሌ ስለ ጂኖች መረጃ (ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፈው ሴሎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚናገር የ DNA ክፍል)።



## ከአስከሬን ምርመራ የታወቀው መረጃ ግላዊ (ሚስጥራዊ) ይሆናል?

**አዎ**፣ ከአስከሬን ምርመራ የታወቀው ነገር ሁሉ ሚስጥራዊ ይሆናል፣ማለትም  ስለ አስከሬን ምርመራው መረጃ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ብቻማየት ይችላሉ።

**መረጃውን ማየት የሚችሉ ሰዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦**

- ሰውየውን የሚንከባከቡ ሐኪሞች
- የአስከሬን ምርመራውን ያካሄዱ ወይም ናሙናዎችን የተመለከቱ ሐኪሞች
- ሌሎች የሰለጠኑ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች
- የRECOVER ጥናት የምርምር ቡድን - ተመራማሪዎቹ በዚህ ጥናት ውስጥ ያገኙትን ለማካፈል ከተናገሩ ወይም በወረቀቶች ቢጽፉ የሞቱትን እና የጥናቱ አካል የሆኑትን ሰዎች የሚለይ መረጃ አያካትቱም።

## ለአስከሬን ምርመራ መክፈል ይኖርብኛል?

**አይ**። ለአስከሬን ምርመራ እርስዎ ወይም ቤተሰብ ምንም አይከፍሉም።

ስለ ሞተው ወዳጅዎ ጥያቄዎችዎን ለመመለስ  እዚህ በRECOVER ውስጥ አለን።

ጥያቄዎችዎን በሚከተለው አድራሻ ኢሜይል ያድርጉልን፦

**RECOVER_Tissue_Pathology@nyulangone.org**

**ወይም በኢሜል መተግበሪያዎ ውስጥ ቀድሞ የተሞላ የኢሜይል ርዕስ እና መልእክት ለማግኘት ይህን የQR ኮድ በስልክዎ ይቃኙ።**

ስለ RECOVER **ጥናት የበለጠ ለማወቅ፣**
**የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ፦**

**RECOVERcovid.org**